# የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ

## የሒሣብ እና የኦዲት ባለሙያዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 1096/2017

ሐምሌ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግቢያ ..... 4

ክፍል አንድ ..... 5

ጠቅላላ ..... 5

1) አጭር ርዕስ ..... 5

2) ትርጓሜ ..... 5

3) የተፈጻሚነት ወሰን ..... 7

ክፍል ሁለት ..... 8

የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች እና አገልግሎት አሰጣጥ ..... 8

4) የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች ..... 8

5) የኦዲት ሙያ ፈቃድ ለያዘ ባለሙያ የተፈቀደ አገልግሎት ..... 8

ክፍል ሦስት ..... 9

ስለ ፈቃድ አሰጣጥ ..... 9

ንዑስ ክፍል አንድ ..... 9

በግል አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ፈቃድ ..... 9

6) የሒሣብ ሥራ አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ..... 9

7) የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ..... 11

8) የፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ..... 14

9) ጣምራ ፈቃድ ..... 16

ንዑስ ክፍል ሁለት ..... 17

የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ፈቃድ ..... 17

10) የሽርክና ማኅበር ስለማቋቋም ..... 17

11) የሽርክና ማኅበር ማቋቋሚያ መስፈርት ..... 17

ንዑስ ክፍል ሦስት ..... 19

ለውጭ አገር ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ፈቃድ ..... 19

12) መርህ ..... 19

13) የኢትዮጵያ ተወላጅ ስለሆነ የውጭ አገር ዜጋ ..... 20

14) የውጪ አገር ዜግነት ያለው ግለሰብ ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ያለበት መስፈርት ..... 20

15) ስለድርጅት ሥያሜ እና በትሥሥር ስለመሥራት ..... 20

ንዑስ ክፍል አራት ........ 21
ስለቅርንጫፍ እና የንግድ ሥያሜ........ 21
16) ቅርንጫፍ ስለመክፈት........ 21
17) ስለ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ ........ 21
18) የሥራ አስኪያጅ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ........ 22
19) የአገልግሎት ክፍያ ........ 22
20) ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ስለመዝጋት........ 22
21) ስለ ንግድ ሥም........ 22
ንዑስ ክፍል አምስት........ 23
የሙያ ፈቃድ ዕድሳት ........ 23
22) የዕድሳት ጊዜ........ 23
23) የሙያ ፈቃድ ለማሳደስ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች ........ 23
24) የማመልከቻ ጊዜው ካለፈ በኋላ ስለሚቀርብ የዕድሳት ጥያቄ ........ 25
25) ያልተሟላ የዕድሳት ማመልከቻ ........ 25
ንዑስ ክፍል ስድስት ........ 26
የሙያ ማኅልበቻ ሥልጠና ........ 26
26) ዓላማ ........ 26
27) ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ........ 26
28) የሙያ ማኅልበቻ ሥልጠና አለመከታተል........ 27
ንዑስ ክፍል ሰባት ........ 27
የአደረጃጀት ለውጥ........ 27
29) ከግል ድርጅት ወደ ሽርክና ማኅበር ለውጥ ስለማድረግ........ 27
30) ከሽርክና ማኅበር ወደ ግል ድርጅት ለውጥ ስለማድረግ........ 28
31) ከኅብረት ሽርክና ማኅበር ወደ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ለውጥ ስለማድረግ........ 29
32) ከሽርክና ማኅበር በመውጣት በግል አገልግሎት ስለመስጠት ........ 29
33) አዲስ ሽሪክ ስለመቀበል ........ 30
34) ከሽርክና ማኅበር በመውጣት በግል ፈቃድ ለማግኘት ማማልከቻ ስለሚቀርብበት ጊዜ........ 31
35) የሙያ ፈቃድ ስለመመለስ ........ 31
ክፍል አራት ........ 32
የባለሙያ ወይም የድርጅት ግዴታዎች እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ........ 32

36) የባለሙያ ወይም የድርጅት ግዴታዎች ..... 32
37) የአስተዳደራዊ እርምጃ አፈጻጸም ..... 34
38) ስለ ሙያ ፈቃድ ዕገዳ ..... 35
39) ወደ ሥራ ስለመመለስ ..... 35
40) የዲሲፕሊን ቅጣት ሪከርድ ..... 36
41) አስተዳደራዊ እርምጃ ..... 36
42) የቅንጅት እና የትብብር ሥራዎች ..... 37
ክፍል አምስት ..... 37
የሒሣብ ሙያ ማኅበራት አክሬዲቴሽን እና ዕውቅና ..... 37
43) በአገር ውስጥ ለተቋቋመ የሒሣብ ሙያ ማኅበር አክሬዲቴሽን ስለመስጠት ..... 37
44) በውጭ አገር ለተቋቋመ የሙያ ማኅበር ዕውቅና ስለመስጠት ..... 38
45) አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ ..... 39
46) አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ይዞ ስለመቀጠል ..... 39
ክፍል ስድስት ..... 40
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ..... 40
47) ክትትል አለማድረግ ..... 40
48) ተመላሽ ስለማይደረግ ክፍያ ..... 40
49) የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ..... 40
50) ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች ..... 41
51) መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ..... 41

# <u>መመሪያ ቁጥር 1096/2017</u>

# <u>የሒሣብ እና የኦዲት ባለሙያዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 1096/2017</u>

## <u>መግቢያ</u>

በአገራችን የካፒታል ገበያ መቋቋምን ተከትሎ የሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጥ ፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ መስጠት የሚያስችል መስፈርት መወሰን በማስፈለጉ፤

በሥራ ላይ ባለው መመሪያ አፈጻጸም ወቅት የታዩ ክፍተቶችን ለመሙላት እና በመመሪያው ውስጥ ያልተሸፈኑ አዲስ ጉዳዮችን ማካተት በማስፈለጉ፤

የሒሳብ እና የኦዲት ሙያ በየጊዜው እየሰፋ እና እያደገ የሚሄድ በመሆኑ ወቅቱን በሚመጥን ባለሙያ ሙያዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማስቻል፤

የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት እና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 አንቀጽ 53(2) እና በቦርዱ ማቋቋሚያ እና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 አንቀጽ 32 መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1) **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የሒሣብ እና የኦዲት ባለሙያዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 1096/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2) **ትርጓሜ**

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1) **"ቦርድ"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ነው፤
2) **"አዋጅ"** ማለት የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ አዋጅ ቁጥር 847/2006 ነው፤
3) **"ደንብ"** ማለት የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ማቋቋሚያና አሠራሩን መወሰኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 332/2007 ነው፤
4) **"የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ"** ማለት ዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌዴሬሽን ወይም እርሱን የሚተካው አካል ከሚያወጣው የሥነ-ምግባር ደንብ ጋር የተጣጣመ የሒሣብ ባለሙያዎች እና ኦዲተሮች የሚመሩበት ቦርዱ ያወጣው ደንብ ነው፡፡
5) **"አባል"** ማለት የዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ሙሉ አባል በሆነ ወይም ቦርዱ አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና በሰጠው የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ ግለሰብ ነው፡፡
6) **"ግዴታውን የተወጣ"** ማለት ባለፉት ሦስት ዓመታት አባል በሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር የዲሲፕሊን እርምጃ ያልተወሰደበት ማለት ነው፡፡
7) **"አግባብነት ያለው ድርጅት"** ማለት በቦርዱ የኦዲት አገልግሎት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው የኦዲት ድርጅት፣ የፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣ የክልል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣ የከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት፣ የሒሣብ ምርመራ አገልግሎት ኮርፖሬሽን ወይም በውጭ አገር የተቋቋመ የኦዲት ድርጅት ነው፡፡
8) **"የአገልግሎት ማስቀጠያ ሥምምነት"** ማለት አንድ የሒሣብ ወይም የኦዲት ባለሙያ በሞት፣ በችሎታ ማጣት፣ ግዴታውን እንዳይፈፅም በሚከለክል ሕመም ወይም ድንገት

ደራሽ ምክንያት የጀመረውን ሥራ መቀጠል ካልቻለ ከቦርዱ የሙያ ፈቃድ በተሰጠው ሌላ ባለሙያ ሥራው እንዲቀጥል ለማድረግ የሚፈጸም ውል ነው፡፡

9) **“ብቁ እና ተገቢ ሰው”** ማለት: -

ሀ) በዕምነት ማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ጥፋተኛ ያልተባለ፣

ለ) በፍርድ ቤት የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት፣

ሐ) በሙያ ሥነ-ምግባር ጉድለት ወይም ጥፋት ምክንያት ንብረት ለማጣራት፣ የሌላን ሰው ንብረት በአደራ ለማስተዳደር፣ የድርጅት ሥራ አስኪያጅ ለመሆን ወይም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል በመሆን ለማገልገል አግባብ ባለው አካል ብቁ አይደለም ያልተባለ፣

መ) አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር በዲሲፕሊን ጥፋት ከአባልነት ያልታገደ ወይም ያልተሰረዘ፣

ሠ) በሕግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የሙያ አገልግሎት እንዳይሰጥ ያልተከለከለ፣

ረ) የሙያ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል አዕምሮአዊ ብቃት ያለው፣

ሰ) ባለፉት ሦስት ዓመታት በማንኛውም ተቋም በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፤ እና

ሸ) የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ተገቢውን የኦዲት ቡድን ያዋቀረ ሰው ነው፡፡

10) **“የኦዲት ሥራ ያልሆነ አገልግሎት”** ማለት፡-

ሀ) ከመዝገብ አያያዝ ወይም ሌሎች ከሒሣብ መዛግብት ወይም ከሒሣብ መግለጫ ዝግጅት ጋር የተያያዙ አገልግሎቶች፣

ለ) የፋይናንስ መረጃ ሥርዓቶች መቅረጽ፣ መዘርጋት እና መተግበር፣

ሐ) የግመታ አገልግሎቶች ወይም በዓይነት የተደረገ መዋጮ ሪፖርቶች ዝግጅት፣

መ) የአክቹወሪ ወይም አስሊ አገልገሎት፣

ሠ) የውስጥ ኦዲት አገልግሎት፣

ረ) የአስተዳደር ተግባራት፣ የሰው ኃይል አስተዳደር እና የደመወዝ ክፍያ የሰነድ ዝግጅት አገልግሎቶች፣

ሰ) የድለላ፣ የአገናኝ ወይም አሻሻጭ፣ የኢንቨስትመንት አማካሪ ወይም የኢንቨስትመንት ባንክ አገልግሎቶች፣

ሸ) ከኦዲት ሥራ ጋር የሚገናኝ የሕግ አገልግሎት፤ ወይም

ቀ) ከግብር ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው፡፡

11) "**ቢሮ**" ማለት የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥበት ስፍራ ሲሆን

ሀ) ቢያንስ ለስድስት ወራት የሚያገለግል ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል የተረጋገጠ እና የተመዘገበ የኪራይ ውል የሚቀርብበት፤ ወይም

ለ) የመንግሥት ንብረት ከሆነ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር የተደረገ የኪራይ ውል የሚቀርብበት፤ ወይም

ሐ) ለንግድ አገልግሎት የሚውል ቢሮ የማከራየት የንግድ ፈቃድ ከተሰጠው የሕንፃ ባለቤት፣ ባንክ፣ ኢንሹራንስ ወይም የሐይማኖት ተቋም ጋር የተደረገ ሥምምነት ከሆነ ቢያንስ ለስድስት ወራት የሚያገለግል ውል የሚቀርብበት፤ ወይም

መ) የግል ንብረት ከሆነ ለንግድ ሥራ ወይም ለቅይጥ አገልግሎት የተፈቀደ እና የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ የሚቀርብበት ነው፡፡

12) "**ጣምራ ፈቃድ**" ማለት የሒሣብ እና የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚያስችል በቦርዱ የሚሰጥ የፈቃድ ዓይነት ነው፡፡

13) በአዋጁ አንቀጽ 2 እና በደንቡ አንቀጽ 2 ሥር የተሰጡ ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## 3) <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ውስጥ የሒሣብ ሥራ ወይም የኦዲት አገልግሎት እንዲሰጡ በቦርዱ ፈቃድ በተሠጣቸው ባለሙያዎች ወይም ድርጅቶች እና በቦርዱ አክሪዲቴሽን ወይም ዕውቅና በተሰጣቸው የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች እና አገልግሎት አሰጣጥ

### 4) የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች

በቦርዱ የሚሰጡ የሙያ ፈቃድ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) የሒሣብ ሥራ አገልግሎት ፈቃድ፣
2) የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ፣
3) የፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ፣ እና
4) ጣምራ ፈቃድ፡፡

### 5) የኦዲት ሙያ ፈቃድ ለያዘ ባለሙያ የተፈቀደ አገልግሎት

1) ከቦርዱ የፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት የሕዝብ ጥቅም ላላበቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች እንዲሁም ለጥቃቅን ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
2) ከቦርዱ የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች እንዲሁም ለጥቃቅን ድርጅቶች የኦዲት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
3) ከቦርዱ የጣምራ ፈቃድ የተሰጠው የፐብሊክ ኦዲተር ወይም የተመሠከረለት ኦዲተር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተጠቀሰው አገልግሎት በተጨማሪ የሕዝብ ጥቅም ላላበቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች እንዲሁም ለጥቃቅን ድርጅቶች የሒሣብ ሥራ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡
4) ከቦርዱ የሒሣብ ሥራ አገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት የሕዝብ ጥቅም ላላበቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት፣ ለአነስተኛ እና መካከለኛ ድርጅቶች እንዲሁም ለጥቃቅን ድርጅቶች የሒሣብ ሥራ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት

# ስለ ፈቃድ አሰጣጥ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## በግል አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ፈቃድ

6) **የሒሣብ ሥራ አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች**

1) የሒሣብ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) ድረስ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሟላቱን ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
3) የሒሣብ ሥራ አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ሰው በደንቡ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ) የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ እና ግዴታውን የተወጣ፤

   ለ) አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያቀረበ፤ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ዓላማ አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ማለት የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል ከመሆኑ በፊት ወይም ከሆነ በኋላ የተገኘ ሆኖ፡-

   1) በማንኛውም ተቋም ውስጥ በሒሣብ ወይም በኦዲት ሥራ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የሠራ፤ ወይም
   2) በፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ሥርዓት ተቆጣጣሪ መንግሥታዊ ተቋም ውስጥ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች ትግበራ ወይም የኦዲት አፈጻጸም ላይ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የምርመራ ሥራ የሠራ እና በሌላ በማንኛውም ተቋም ውስጥ ለተጨማሪ አንድ ዓመት የሒሣብ ወይም የኦዲት ሥራ የሠራ፤ ወይም

3) በግልም ሆነ በመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የአካውንቲግ ኮርሶችን ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ያስተማረ እና በሌላ በማንኛውም ተቋም ውስጥ ለተጨማሪ አንድ ዓመት የሒሣብ ወይም የኦዲት ሥራ የሠራ ነው፡፡

4) በዚህ የንዑስ ንዑስ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምዶች በውጭ አገር የተገኙ ከሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ቢያንስ ለአንድ ዓመት የሒሣብ ወይም የኦዲት ሥራ የሠራ መሆን አለበት፡፡

ሐ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ስለመሆኑ መጨረሻ ከሠራበት ድርጅት የተሰጠ ማረጋገጫ፤

መ) ብቁ እና ተገቢ ሰው ስለመሆኑ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

ሠ) የብር አምስት መቶ ሺህ (500 ሺህ) የሙያ መድን የገንዘብ ዋስትና መግባት፤

ረ) የአገልግሎት ማስቀጠያ ሥምምነት ውል ማቅረብ፤

ሰ) መጨረሻ ከሠራበት ተቋም የሥራ ስንብት ደብዳቤ ማቅረብ፤

ሸ) የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ማቅረብ፤ እና

ቀ) በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው የፓስፖርት መጠን ያለው ባለቀለም አንድ ፎቶግራፍ ማቅረብ አለበት፡፡

4) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ በቦርዱ ሲረጋገጥ አመልካቹ የሥራ ስንብት ደብዳቤ፣ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ እና አንድ ፎቶግራፍ ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም አመልካቹ የሒሣብ አገልግሎት በሚሰጥ የሽርክና ማኅበር ውስጥ ተቀጣሪ ከሆነ እና ወደ ሽሪክነት የሚያድግ ከሆነ የሥራ ሥንብት ደብዳቤ ወይም ማኅበሩ በሽሪክነት ሊቀበለው መስማማቱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ ይችላል፡፡

5) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረቡ በቦርዱ ሲረጋገጥ የአመልካቹን ሥም እና አድራሻ በሒሣብ ባለሙያዎች መዝገብ ላይ በማስፈር የሙያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሙያዊ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የሙያ መድን ዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ፣ የአገልግሎት ማስቀጠያ ስምምነት ሰነድ እና ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከቦርዱ ፈቃድ በተሰጠው የሽርክና ማኅበር ውስጥ ሽሪክ በመሆን አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ሥር የተጠቀሱትን ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገጉትን መስፈርቶች በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማሟላት አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት መቅረብ የሚገባው ማስረጃ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ የባለሙያው የሙያ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡ የሙያ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሙያ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል እንደ አዲስ ማመልከት ይችላል፡፡

## 7) <u>የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች</u>

1) የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሟላቱን ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
3) የተመሠከረለት ኦዲተር በመሆን አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ሰው በደንቡ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 3 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ) የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ እና ግዴታውን የተወጣ፤

   ለ) አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር ሁሉንም የኦዲት እና ማረጋገጥ ትምህርቶች መውሰድ እና የተሰጠውን ፈተና ማለፍ፤

ሐ) አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር የፀና የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት ማቅረብ፤ አመልካቹ አባል የሆነበት ማኅበር ባለው አሰራር የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት የማይሰጥ ከሆነ ቦርዱ ለዚሁ አገልግሎት ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

መ) አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ማቅረብ፤ ለዚህ ንዑስ አንቀጽ ዓላማ አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ማለት የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል ከሆነ በኋላ የተገኘ ሆኖ፡-

1) አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት በኦዲተርነት የሠራ እና ከዚህ ውስጥ ለአንድ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት ወይም ሥራ አስኪያጅነት የሠራ፤ ወይም

2) የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀትና አቀራረብ ሥርዓት ተቆጣጣሪ መንግስታዊ ተቋም ውስጥ የፋይናንስ ሪፖርት ደረጃዎች ትግበራ ወይም የኦዲት አፈጻጸም ላይ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የምርመራ ሥራ የሠራ እና አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለተጨማሪ አንድ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት ወይም ሥራ አስኪያጅነት የሠራ፤ ወይም

3) በግልም ሆነ በመንግሥት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የአካውንቲግ ኮርሶችን ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ያስተማረ እና አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለተጨማሪ አንድ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት ወይም ሥራ አስኪያጅነት የሠራ፤ ወይም

4) በውስጥ ኦዲተርነት ቢያንስ ለሦስት ዓመታት የሠራ እና አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለተጨማሪ አንድ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት ወይም ሥራ አስኪያጅነት የሠራ፤

5) በዚህ የንዑስ ንዑስ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት የሥራ ልምዶች በውጭ አገር የተገኙ ከሆነ በቦርዱ ፈቃድ በተሰጠው የኦዲት ድርጅት ውስጥ ቢያንስ ለአንድ ዓመት በኦዲት ማናጀርነት ወይም ሥራ አስኪያጅነት የሠራ መሆን አለበት፡፡

ሠ) መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ስለመሆኑ መጨረሻ ከሠራበት ድርጅት የተሰጠ ማረጋገጫ፤

ረ) ብቁ እና ተገቢ ሰው ስለመሆኑ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

ሰ) የብር አንድ ሚሊዮን (1,000,000.00) የሙያ መድን የገንዘብ ዋስትና መግባት፤

ሸ) ቢያንስ አንድ የኦዲት ቡድን ማዋቀር፤ ቡድኑ በአካውንቲንግ፣ በኦዲቲንግ እና ተያያዥ በሆነ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው የኦዲት ማኔጀር፣ ከፍተኛ እና ጀማሪ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የኦዲት ማኔጀሩ እና ከፍተኛ ባለሙያው እንደ ቅደም ተከተላቸው ቢያንስ ለሦስት እና ለሁለት ዓመታት አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ በኦዲተርነት የሠሩ መሆን አለባቸው፤ የኦዲት ቡድኑ ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጠውን ባለሙያ ሊያካትት ይችላል፤ እና

ቀ) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(3) ከፊደል ተራ (ረ) እስከ (ቀ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

4) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ በቦርዱ ሲረጋገጥ አመልካቹ መጨረሻ ከሠራበት ተቋም የሥራ ስንብት ደብዳቤ፣ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ፤ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳው የፓስፖርት መጠን ያለው ባለቀለም አንድ ፎቶግራፍ ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም አመልካቹ የኦዲት አገልግሎት በሚሰጥ ሽርክና ማኅበር ውስጥ ተቀጣሪ የሆነ እና ከተቀጣሪነት ወደ ሽሪክነት የሚያድግ ከሆነ የሥራ ሥንብት ደብዳቤ ወይም ማኅበሩ በሽሪክነት ሊቀበለው መስማማቱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ ይችላል፡፡

5) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ረ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረቡ በቦርዱ ሲረጋገጥ የአመልካቹን ሥም እና አድራሻ በተመሠከረላቸው ኦዲተሮች መዝገብ ላይ በማስፈር የሙያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሙያዊ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የሙያ መድን ዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ፣ የኦዲት ቡድን፣ የአገልግሎት ማስቀጠያ ስምምነት ሰነድ እና ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከቦርዱ ፈቃድ በተሰጠው የሽርክና ማኅበር ውስጥ ሽሪክ በመሆን አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ሥር የተጠቀሱትን ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ

አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገጉትን መስፈርቶች በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማሟላት አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት መቅረብ የሚገባው ማስረጃ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ የባለሙያው የሙያ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡ የሙያ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሙያ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል እንደ አዲስ ማመልከት ይችላል፡፡

8) <u>የፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች</u>

1) የሕዝብ ጥቅም ላለባቸው ሪፖርት አቅራቢ አካላት የኦዲት ሥራ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ የተመሠከረለት ኦዲተር ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከት ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሰ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሟላቱን ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሰረት መቅረብ አለበት፡፡

3) ፐብሊክ ኦዲተር በመሆን አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 18 የተቀመጡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ) ከአምስት ላላነሱ ዓመታት ሳያቋርጥ የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል የሆነ እና ግዴታውን የተወጣ፤

   ለ) አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር ሁሉንም የኦዲት እና ማረጋገጥ ትምህርቶች መውሰድ እና የተሰጠውን ፈተና ማለፍ፤

   ሐ) አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር የፀና የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት ማቅረብ፤ አመልካቹ አባል የሆነበት ማኅበር ባለው አሰራር የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት የማይሰጥ ከሆነ ቦርዱ ለዚሁ አገልግሎት ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

   መ) ከቦርዱ የተሰጠ የፀና የኦዲት ፈቃድ ማቅረብ እና ቢያንስ ላለፉት ሦስት ዓመታት በግል ወይም በሽርክና የኦዲት ሥራ አገልግሎት መስጠት፤

   ሠ) ብቁ እና ተገቢ ሰው ስለመሆኑ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

ረ) ቦርዱ ባከናወነው የኦዲት ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ውጤት ወይም በክስ ሰሚ ችሎት ማስተካከያ እንዲያደርግ የተሰጠውን አስተያየት ወይም ትዕዛዝ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማስተካከል ቁርጠኛ ሆኖ እየሰራ ስለመሆኑ ከቦርዱ ማስረጃ ማቅረብ፤

ሰ) የኦዲት ደረጃዎች እና የጥራት አመራር ሥርዓት በአግባቡ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ መተግበራቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቴክኖሎጂ እና ተገቢ ሶፍትዌሮችን በሁለት ዓመታት ውስጥ በሥራ ላይ ለማዋል የፅሁፍ ማረጋገጫ ማቅረብ፤

ሸ) ቢያንስ ሁለት የኦዲት ቡድን ማዋቀር፤ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የተመሠከረለት የሒሣብ ባለሙያ የሆነ እና ቢያንስ ለአንድ ዓመት አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ በኦዲተርነት የሠራ የኦዲት ማናጀር፤ በአካውንቲንግ፣ በኦዲቲንግ እና ተያያዥ በሆነ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ከፍተኛ እና ጀማሪ ባለሙያ፤ ከፍተኛ ባለሙያው ለሁለት ዓመታት አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ በኦዲተርነት የሠራ መሆን አለበት፡፡ የኦዲት ቡድኑ ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጠውን ባለሙያ ሊያካትት ይችላል፡፡

ቀ) የብር ሦስት ሚሊዮን (3,000,000.00) የሙያ መድን ዋስትና መግባት፤

በ) የብር አንድ ሚሊዮን (1,000,000.00) የተመዘገበ የመሥሪያ ካፒታል ማቅረብ፤ እና

ተ) የአገልግሎት ማስቀጠያ ሥምምነት ውል ማቅረብ አለበት፡፡

4) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሰ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ በቦርዱ ሲረጋገጥ አመልካቹ ቀደም ሲል ከቦርዱ የተሰጠውን የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ ዋናውን መመለስ አለበት፡፡

5) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሰ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረቡ በቦርዱ ሲረጋገጥ የአመልካቹን ሥም እና አድራሻ በፐብሊክ ኦዲተሮች መዝገብ ላይ በማስፈር የሙያ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ሙያዊ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የሙያ መድን ዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ፣ የኦዲት ቡድን፣ የአገልግሎት ማስቀጠያ ስምምነት ሰነድ እና ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከቦርዱ ፈቃድ በተሰጠው የሽርክና ማኀበር ውስጥ ሽሪክ በመሆን አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 ሥር የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች እንዲያቀርብ አይገደድም፡፡ ሆኖም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር የተደነገጉትን መስፈርቶች በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማሟላት አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀጽ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 እና 7 መሠረት መቅረብ የሚገባውን ማስረጃ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የሙያ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡ የሙያ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሙያ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል እንደ አዲስ ማመልከት ወይም የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃዱ እንዲመለስለት በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡

9) <u>ጣምራ ፈቃድ</u>

1) የፐብሊክ ኦዲተር ወይም የተመሠከረለት ኦዲተር ፈቃድ ያለው ባለሙያ ወይም ድርጅት ከሚሰጠው የኦዲት አገልግሎት በተጨማሪ የሒሣብ ሥራ አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ከሆነ የጣምራ ፈቃድ እንዲሰጠው ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
3) ቦርዱ የቀረበለውን ማመልከቻ በመገምገም የሒሣብ እና የኦዲት አገልግሎት በጣምራ መሥጠት የሚያስችል የሙያ ፈቃድ ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡
4) ማንኛውም ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው ፐብሊክ ኦዲተር ወይም የተመሠከረለት ኦዲተር የጣምራ ፈቃድ ሳይዝ የሒሣብ ሥራ አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡
5) አመልካቹ ከቦርዱ የተሰጠ ፈቃድ ሳይኖረው ጣምራ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት ከሆነ እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ ለተመሠከረለት ኦዲተር ወይም ለፐብሊክ ኦዲተር የተቀመጠውን መስፈርት በቅድሚያ ማሟላት አለበት፡፡

6) የጣምራ ፈቃድ ያለው የኦዲት ድርጅት ወይም የድርጅቱ ሽሪክ ጉልህ ጥቅም ያለበት ድርጅት፣ የኦዲት ሥራ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ለደንበኛው በሰጠበት የሒሣብ ዓመት የኦዲት ሥራ አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ፈቃድ</u>

### 10)<u>የሽርክና ማኅበር ስለማቋቋም</u>

1) ከቦርዱ የተሰጠ የፀና የሙያ ፈቃድ ያላቸው ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ባለሙያዎች አንድ ላይ በመሆን የሽርክና ማኅበር ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2) ከቦርዱ የሒሣብ ወይም የኦዲት ፈቃድ የተሰጣቸው ባለሙያዎች የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት መስጠት የሚችሉት በተመሳሳይ ዘርፍ ፈቃድ ከተሰጣቸው ባለሙያዎች ጋር ብቻ ነው፡፡

### 11)<u>የሽርክና ማኅበር ማቋቋሚያ መስፈርት</u>

1) የሽርክና ማኅበር በማቋቋም የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ባለሙያዎች ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሟላቱን ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
3) የሽርክና ማኅበር በማቋቋም የሙያ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ባለሙያዎች በአዋጁ አንቀጽ 21 እና በደንቡ አንቀጽ 20 ሥር ከተቀመጡት መስፈርቶች በተጨማሪ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማሟላት አለባቸው፡-

   ሀ) የሽሪኮቹን ሙሉ ሥም እና ፊርማ የያዘ ማመልከቻ ማቅረብ፣

   ለ) ከቦርዱ የተሰጣቸውን የእያንዳንዱን ሽሪክ የፀና የሙያ ፈቃድ ማቅረብ ፣

   ሐ) የመመስረቻ ጽሁፍ ማቅረብ፣

   መ) በቦርዱ ተቀባይነት ያለው የድርጅት ሥም ማቅረብ፣

   ሠ) የሙያ መድን ዋስትና ውል መግባት፤

1) የሒሣብ አገልግሎት ለመስጠት የሚቋቋም ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ከሆነ አንድ ሚሊዮን (1,000,000.00) ፤ የኅብረት ሽርክና ማኅበር ከሆነ የብር አምስት መቶ ሺህ (500,000.00) ፤

2) በተመሠከረለት ኦዲተር የሚቋቋም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ከሆነ የብር ሁለት ሚሊዮን (2,000,000.00) ፤ የኅብረት ሽርክና ማኅበር ከሆነ የብር አንድ ሚሊዮን (1,000,000.00) ፤

3) በፐብሊክ ኦዲተር የሚቋቋም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ከሆነ የብር አምስት ሚሊዮን (5,000,000.00) ፤ የኅብረት ሽርክና ማኅበር ከሆነ የብር ሦስት ሚሊዮን (3,000,000.00) ፤

ረ) የኦዲት ቡድን ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ፤

1) በተመሠከረለት ኦዲተር የሚቋቋም ኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ የኦዲት ድርጅት ከሆነ ቢያንስ አንድ የኦዲት ቡድን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤ በቡድኑ ውስጥ በአካውንቲንግ፣ በኦዲቲንግ እና ተያያዥ በሆነ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው የኦዲት ማኔጀር፣ ከፍተኛ እና ጀማሪ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የኦዲት ማኔጀሩ እና ከፍተኛ ባለሙያው እንደ ቅደም ተከተላቸው ለሦስት እና ለሁለት ዓመታት አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ በኦዲተርነት የሠሩ መሆን አለባቸው፡፡ የኦዲት ቡድኑ ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጠውን ባለሙያ ሊያካትት ይችላል፡፡

2) በፐብሊክ ኦዲተር የሚቋቋም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ የኦዲት ድርጅት ከሆነ ቢያንስ ሁለት የኦዲት ቡድን ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤ በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ በአካውንቲንግ፣ በኦዲቲንግ እና ተያያዥ በሆነ የትምህርት ዘርፍ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው የኦዲት ማኔጀር፣ ከፍተኛ እና ጀማሪ ባለሙያ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የኦዲት ማኔጀሩ እና ከፍተኛ ባለሙያው እንደ ቅደም ተከተላቸው ለአምስት እና ለሦስት ዓመታት አግባብነት ያለው ድርጅት ውስጥ በኦዲተርነት የሠሩ መሆን አለባቸው፡፡ የኦዲት ቡድኑ ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጠውን ባለሙያ ሊያካትት ይችላል፡፡

ሰ) በፐብሊክ ኦዲተር የሚቋቋም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ የኦዲት ድርጅት ከሆነ የብር አንድ ሚሊዮን (1,000,000.00) የተመዘገበ የመሥሪያ ካፒታል ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤ እና

ሸ) ስድስት ወር ያላለፈው የፓስፖርት መጠን ያለው የሥራ አስኪያጅ ባለቀለም ፎቶ ግራፍ ማቅረብ አለበት፡፡

4) አመልካቾች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸው በቦርዱ ሲረጋገጥ አመልካቾች ቀደም ሲል ከቦርዱ የተሰጣቸውን የሙያ ፈቃድ ዋናውን መመለስ አለባቸው፡፡

5) አመልካቾች በዚህ አንቀጽ ንዐስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ (ሀ) እስከ (መ) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ሥር የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረባቸው በቦርዱ ሲረጋገጥ የአመልካቾቹን የድርጅት ሥም እና አድራሻ በድርጅቶች መዝገብ ላይ በማስፈር ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽ መሠረት የተመዘገበ ድርጅት ሙያው አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የሙያ መድን ዋስትና ማረጋገጫ ሰነድ፣ እንደአግባብነቱ የኦዲት ቡድን እና ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

7) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት መቅረብ የሚገባውን ማስረጃ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ቦርዱ ምዝገባውን ይሰረዛል፡፡ ምዝገባው ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ የድርጅቱ ሽሪኮች ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል እንደ አዲስ ማመልከት ወይም ቀድሞ የነበራቸው ፈቃድ እንዲመለስላቸው በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማመልከት ይችላል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሦስት</u>

## <u>ለውጭ አገር ባለሙያዎች ስለሚሰጥ ፈቃድ</u>

12)<u>**መርህ**</u>

1) ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ሰው ጋር የሽርክና ማህበር በማቋቋም የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡ ሆኖም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 474/2012 አንቀጽ 5 መሠረት የውጪ

አገር ዜግነት ያለው ግለሰብ በማኅበሩ ላይ ሊኖረው የሚችለው ድርሻ ከ49 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

2) የውጭ አገር ዜግነት ባለው እና ኢትዮጵያዊ በሆነ ባለሙያ ወይም ድርጅት በጥምረት የሚቋቋመው የሽርክና ማኅበር ሥራ አስኪያጅ መሆን የሚችለው ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሽሪክ ነው፡፡

13)<u>የኢትዮጵያ ተወላጅ ስለሆነ የውጭ አገር ዜጋ</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች፣ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ በወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 መሠረት እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና ሁለት መሠረት ይስተናገዳሉ፡፡

14)<u>የውጪ አገር ዜግነት ያለው ግለሰብ ፈቃድ ለማግኘት ማሟላት ያለበት መስፈርት</u>

1) የውጪ አገር ዜግነት ያለው ግለሰብ ከቦርዱ የሒሣብ ወይም የኦዲት ፈቃድ ለማግኘት እንደአግባብነቱ በአዋጁ አንቀጽ 18፣ በደንቡ አንቀጽ 17 እና 18 እንዲሁም በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ ሥር የተደነገጉትን መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡
2) አመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሰውን መስፈርት ማሟላቱ በቦርዱ ሲረጋገጥ የሽርክና ማኅበር ማቋቋም የሚያስችል ጊዜያዊ የምሥክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
3) በዚህ አንቀጽ መሠረት ጊዜያዊ የምሥክር ወረቀት የተሰጠው ግለሰብ የምሥክር ወረቀቱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ በቦርዱ ፈቃድ ከተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት ጋር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሠረት የሽርክና ማኅበር ማቋቋም አለበት፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ የሽርክና ማኅበር በማቋቋም ማስረጃ ለቦርዱ ካላቀረበ የምሥክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

15)<u>ስለድርጅት ሥያሜ እና በትሥሥር ስለመሥራት</u>

ማንኛውም የኦዲት ድርጅት የድርጅቱ ሥም ከክልላዊው ወይም ዓለም አቀፋዊ የኦዲት ኔትዎርክ ሥም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ወይም የኔትወርኩን ሥም የሚያካትት ከሆነ ወይም

የድርጅቱ ባለዓርማ ወረቀት ወይም ማንኛውም ሰነድ የኔትወርኩ አካል መሆኑን የሚያመላክት ከሆነ በሥሙ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት ለቦርዱ የማሳወቅ እና የሚከተሉትን ማስረጃዎች የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

1) በኦዲት ድርጅቱ እና በክልላዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ድርጅቱ መካከል የተደረገውን ውል፤ እና
2) በዓለም አቀፍ የጥራት አመራር ደረጃዎች መሠረት የተዘጋጀ የአሠራር ሥርዓት ወይም ማንዋል።

## <u>ንዑስ ክፍል አራት</u>

## <u>ስለቅርንጫፍ እና የንግድ ሥያሜ</u>

### 16)<u>ቅርንጫፍ ስለመከፈት</u>

1) ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በመክፈት አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
3) በዚህ አቀንጽ መሠረት ቅርንጫፍ የሚከፍት ባለሙያ ወይም ድርጅት ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ እና ቅርንጫፍ በሚከፍትበት ሥፍራ ንግድ ፈቃድ እንዲያወጣ የሚገደድ ከሆነ የንግድ ፈቃድ ቅጂ ማቅረብ አለበት፡፡

### 17)<u>ስለ ቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ</u>

1) ማንኛውም ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ ሊኖረው ይገባል፡፡
2) ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት ለቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት የሾመውን ወይም የቀጠረውን ሥራ አስኪያጅ ቅጥሩ በተፈጸመ በ14 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።
3) የቅርንጫፉ ሥራ አስኪያጅ የሒሣብ ሙያ ማኅበር አባል ከሆነ በቅድሚያ ቦርዱን በጽሁፍ በማሳወቅ በሒሣብ መግለጫ ወይም በኦዲት ሪፖርት ላይ እንዲፈርም በባለሙያው ወይም በድርጅቱ ሥልጣን ሊሰጠው ይችላል፡፡

4) የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሥራ አስኪያጅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ለሚያከናውነው ተግባር ሙሉ ኃላፊነቱን የሚወስደው ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት ነው፡፡

18)**<u>የሥራ አስኪያጅ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ</u>**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በሒሣብ መግለጫ ወይም በኦዲት ሪፖርት ላይ እንዲፈርም ሥልጣን የተሰጠው ሥራ አስኪያጅ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል ስድስት ሥር በተደነገገው መሠረት በየዓመቱ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና መውሰድ አለበት፡፡

19)**<u>የአገልግሎት ክፍያ</u>**

ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት ለሚከፍተው ለእያንዳንዱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት በየዓመቱ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

20)**<u>ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ስለመዝጋት</u>**

ባለሙያው ወይም ድርጅቱ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን ከዘጋ በ14 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

21)**<u>ስለ ንግድ ሥም</u>**

1) የንግድ ሥም ያለው ባለሙያ ወይም ድርጅት ቦርዱ በየጊዜው በሚያወጣው የባለሙያዎች ዝርዝር ላይ ከድርጅት ሥያሜው በተጨማሪ የንግድ ሥሙ እንዲካተትለት ሊያመለክት ይችላል፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከአገልግሎት ክፍያ ደረሠኝ እና የንግድ ሥሙ በሚመለከተው የመንግሥት አካል የተመዘገበ መሆኑን ከሚያረጋግጥ ማስረጃ ጋር መቅረብ አለበት፡፡
3) ቦርዱ የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ መመሪያ እና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የአመልካቹ የንግድ ሥም በየጊዜው ይፋ በሚደረገው የባለሙያዎች ዝርዝር ላይ እንዲካተት ያደርጋል፡፡
4) ቦርዱ ይፋ በሚያደርገው የባለሙያዎች ዝርዝር ውስጥ የንግድ ሥያሜ እንዲካተትለት የሚፈልግ ባለሙያ ወይም ድርጅት በየዓመቱ የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

5) በባለሙያዎች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ከተደረገ የንግድ ሥም በስተቀር ከንግድ ሥም ጋር በተያየዘ ለሦስተኛ ወገን ቦርዱ ማረጋገጫ እንዲሰጥ የሚቀርብ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም፡፡

## ንዑስ ክፍል አምስት

## የሙያ ፈቃድ ዕድሳት

22)**የዕድሳት ጊዜ**

1) በቦርዱ የተሰጠ የሙያ ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡
2) የተሰጠበት ቀን ግምት ውስጥ ሳይገባ የሙያ ፈቃድ የሚፀናው በየዓመቱ እስከ ጥር ሰላሳ ድረስ ነው፡፡
3) የሙያ ፈቃድ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት የእድሳት ማመልከቻ መቅረብ ይችላል፡፡
4) የአገልግሎት ጊዜው ካበቃ በኋላ የሚቀርብ የእድሳት ማመልከቻ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 መሠረት በቅጣት ይስተናገዳል፡፡
5) በማንኛውም ሁኔታ ሳይታደስ አንድ ዓመት ያለፈው የሙያ ፈቃድ ይሰረዛል፡፡
6) ባለሙያው ፈቃዱን ያላሳደሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ፈቃዱ እንዲመለስለት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡ ማመልከቻው ከደጋፊ ማስረጃ ጋር መቅረብ አለበት፡፡
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የቀረበ ማመልከቻ በዋና ዳይሬክተሩ ተቀባይነት ካገኘ ባለሙያው የዕድሳት አገልግሎት ክፍያ እና ዕድሳቱ ለዘገየበት ቅጣት እንዲከፈል ተደርጎ ፈቃዱ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የቅጣት መጠኑ ሲሰላ ባለሙያው ባጋጠመው ችግር ምክንያት ማመልከቻ ማቅረብ ያልቻለበት ጊዜ ተቀናሽ ሊደረግ ይችላል። ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ የቅጣት መጠኑ ከአንድ ዓመት ቅጣት መብለጥ የለበትም፡፡

23)**የሙያ ፈቃድ ለማሳደስ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች**

ከቦርዱ የሒሣብ ወይም የኦዲት ሙያ ፈቃድ የወሰደ ባለሙያ ወይም ድርጅት ፈቃዱን ለማሳደስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፡፡

1) ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት የእድሳት ማመልከቻ እና የአገልግሎት ክፍያ ደረሠኝ፤

2) ባለሙያው ወይም እያንዳንዱ ሽሪክ እንዲሁም በሒሣብ መግለጫ ወይም በኦዲት ሪፖርት ላይ የመፈረም ሥልጣን የተሰጠው የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር የአባልነት ግዴታውን የተወጣ ስለመሆኑ ማረጋገጫ፤ ይህ ድንጋጌ አባል ከሆኑበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር የፀና የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት የሚያቀርቡ ባለሙያዎች አይመለከትም፤

3) የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ከሆነ እንደአግባብነቱ ባለሙያው ወይም እያንዳንዱ ሽሪክ የፀና የሙያ ሥራ የምስክር ወረቀት፤

4) ባለሙያው ወይም እያንዳንዱ ሽሪክ እንዲሁም በሒሣብ መግለጫ ወይም በኦዲት ሪፖርት ላይ የመፈረም ሥልጣን የተሰጠው የቅርንጫፍ ሥራ አስኪያጅ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል ስድስት ሥር የተቀመጠውን የሥልጠና ግዴታ ማጠናቀቁን የሚገልጽ ማስረጃ፤

5) ፈቃድ ለማግኘት በተቀመጠው መጠን የፀና የሙያ መድን ዋስትና፤

6) በግል የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የፀና የአገልግሎት ማስቀጠያ ስምምነት፤

7) በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት የነበሩ የደንበኞች ዝርዝር፣ የተሰጠ የአገልግሎት ዓይነት፣ ለአገልግሎቱ የተከፈለው የክፍያ መጠን፣ ሥራውን ያከናወነው ሽሪክ ወይም ፈራሚ ሥም እንዲሁም ቦርዱ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ያካተተ ሰነድ፤

8) የድርጅቱን ዓመታዊ የሒሣብ መግለጫ፣

9) የኦዲት ድርጅት ከሆነ በዓለም አቀፍ የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ደረጃ መሠረት የኦዲት ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት ስለመተግበሩ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

10) የፀና ንግድ ፈቃድ፤

11) ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ፤

12) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(3) (መ)፣ (ሸ) እና (ቀ) ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች፤ እና

13) የውጭ አገር ዜግነት ባለው እና ኢትዮጵያዊ በሆነ ባለሙያ ወይም ድርጅት በጥምረት የተቋቋመ የሽርክና ማኅበር ከሆነ በዚህ አንቀጽ ከተደነገጉት መስፈርቶች በተጨማሪ

የውጭ አገር ዜግነት ያለው ሽሪክ የፀና የመኖሪያ ፈቃድ እና የፀና የሥራ ፈቃድ መቅረብ አለበት፡፡

24)**<u>የማመልከቻ ጊዜው ካለፈ በኋላ ስለሚቀርብ የዕድሳት ጥያቄ</u>**

የሙያ ፈቃዱ የአገልግሎት ጊዜ ካበቃ በኋላ የሚቀርብ የእድሳት ማመልከቻ፡-

1) በግል የሒሣብ ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ከሆነ ዕድሳቱ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ሦስት መቶ (300) ብር፤
2) በሽርክና የሒሣብ ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ከሆነ ዕድሳቱ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ስድስት መቶ (600) ብር፤
3) በግል የኦዲት ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ከሆነ ዕድሳቱ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ስድስት መቶ (600) ብር፤
4) በሽርክና የኦዲት ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት ከሆነ ዕድሳቱ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ዘጠኝ መቶ (900) ብር፤

ቅጣት በመክፈል ሊታደስ ይችላል፡፡

25)**<u>ያልተሟላ የዕድሳት ማመልከቻ</u>**

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ሥር የተዘረዘረው መስፈርት ሳይሟላ የቀረበ የዕድሳት ማመልከቻ በሰላሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተሟልቶ ካልቀረበ ማመልከቻው ውድቅ ይደረጋል፡፡ ሰላሳ ቀኑ መቆጠር የሚጀምረው ማመልከቻው በቦርዱ ታይቶ አስተያየት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በቦርዱ እንዲሟላ የተጠየቀው ማስረጃ ሙሉ ለሙሉ ተጠቃሎ በአንድ ቀን መቅረብ አለበት፡፡ በተለያየ ቀን ተነጣጥሎ የሚቀርብ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም፡፡
3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የዕድሳት ማመልከቻው ውድቅ የተደረገበት ባለሙያ ወይም ድርጅት ለእድሳት የሚከፈለውን የአገልግሎት ክፍያ በድጋሚ በመክፈል ሊያመለክት ይችላል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት የሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 መሠረት የሚከፈለውን የቅጣት ክፍያ አያስቀርም፡፡

## ንዑስ ክፍል ስድስት

## የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና

### 26)ዓላማ

የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና ዓላማ ባለሙያዎች የሙያ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ወቅታዊ ዕውቀት እና ክህሎት በቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

### 27)ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ

1) ማንኛውም ባለሙያ በዓመት ውስጥ ቢያንስ አርባ ሰዓት ወይም ዩኒት ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ሥር ከተጠቀሰው የሥልጠና ጊዜ ውስጥ ሃያው ሰዓት ወይም ዩኒት በማስረጃ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም አንድ ዩኒት ማለት አንድ ሰዓት ነው፡፡
3) አባል ከሆነበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር የፀና የሙያ ሥራ የምሥክር ወረቀት የሚያቀርብ ባለሙያ ከሚጠበቅበት የአርባ ሰዓት ወይም ዩኒት የሙያ ማጎልበቻ የሥልጠና ግዴታ ውስጥ መውሰድ ያለበት ማስረጃ የሚቀርብበትን የሃያ ሰዓት ወይም ዩኒት ሥልጠና ብቻ ነው፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ባለሙያው ማስረጃ እንዲያቀርብ የሚገደድበት ሥልጠና መወሰድ ያለበት ቦርዱ በእራሱ ወይም ከሌሎች ጋር በመተባበር የሰጠው ሥልጠና መሆን አለበት፡፡
5) በቦርዱ ከሚሰጠው ሥልጠና ውጪ ተቀባይነት የሚኖረው የሥልጠና ዓይነት ቦርዱ በሚያወጣው ፖሊሲ ይወሰናል፡፡
6) የሥልጠና ዘርፍ፣ የሥልጠና አሰጣጥ መርሐ-ግብር፣ የሥልጠና ክፍያ እና ሌሎች ከሥልጠና ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በተመለከተ ቦርዱ በየጊዜው በሚያወጣው ማስታወቂያ ይገለጻል፡፡
7) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በቦርዱ ካልተፈቀደለት በስተቀር የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና የመውሰድ ግዴታውን ያልተወጣ ባለሙያ የሙያ ፈቃዱ አይታደስለትም፡፡

## 28)<u>የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና አለመከታተል</u>

1) ማንኛውም ባለሙያ በአሳማኝ ምክንያት ቦርዱ በሚያወጣው መርሐ-ግብር መሠረት ሥልጠና መውሰድ ካልቻለ ቦርዱ ከያዘው የሥልጠና ጊዜ ከአስራ አምስት ተከታታይ ቀናት በፊት ለቦርዱ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት፡፡
2) ባለሙያው የሚያቀርበው ማመልከቻ ሥልጠናውን መውሰድ እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት፣ በቀጣይ መቼ እና በምን አግባብ መውሰድ እንደሚችል የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
3) ባለሙያው ያቀረበው ማመልከቻ በቦርዱ አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ የሥልጠና ጊዜውን በዚያው ዓመት ውስጥ ባለሙያው በጠየቀው ጊዜ ወይም ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ሊቀይርለት ይችላል፡፡ ቦርዱ ጥያቄውን የተቀበለው ወይም ያልተቀበለው መሆኑን በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሙያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
4) ባለሙያው በዓመት ውስጥ መውሰድ የሚጠበቅበትን ሥልጠና በዚያው ዓመት መውሰድ ካልቻለ እና ሥልጠናውን ያልወሰደው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የቦርዱ ዋና ዳይሬክተር ካመነበት ባለሙያው ያልወሰደውን የሥልጠና ሰዓት ወደ ቀጣይ ዓመት በማሸጋገር በቀጣይ ዓመት መውሰድ ከሚጠበቅበት የሥልጠና ግዴታ ጋር እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሰባት</u>

## <u>የአደረጃጀት ለውጥ</u>

## 29)<u>ከግል ድርጅት ወደ ሽርክና ማኅበር ለውጥ ስለማድረግ</u>

1) የግል ድርጅት በማቋቋም የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ባለሙያዎች የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት መስጠት ከፈለጉ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ባለሙያዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡
    ሀ) ከቦርዱ የተሰጣቸውን የእያንዳንዳቸውን የፀና የሙያ ፈቃድ ዋናውን መመለስ፣
    ለ) የግል ድርጅታቸውን ስለመዝጋታቸው ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፣

ሐ) የግል ድርጅታቸውን ለመዝጋት ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ እስከቀረበበት ቀን ድረስ የሚጠበቅባቸውን ግብር ስለመክፈላቸው የማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ፤

መ) የሙያ ፈቃዳቸው ተመላሽ ከተደረገ በኋላ በየግላቸው አገልግሎት የማይሰጡ ስለመሆኑ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

ሠ) የሙያ ፈቃዱን በመለሱበት በጀት ዓመት እያንዳንዳቸው የነበሯቸውን የደንበኞችን ዝርዝር፣ የሰጡት የአገልግሎት ዓይነት እና ቦርዱ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ያካተተ ሰነድ ማቅረብ፤ እና

ረ) የሽርክና ማኅበር በማቋቋም የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል ሁለት ሥር የተቀመጡ መስፈርቶችን እንደአግባብነቱ ማሟላት አለባቸው፡፡

## 30)<u>ከሽርክና ማኅበር ወደ ግል ድርጅት ለውጥ ስለማድረግ</u>

1) የሽርክና ማኅበር በማቋቋም የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ባለሙያዎች ማኅበሩን በማፍረስ በየግላቸው አገልግሎት መስጠት ከፈለጉ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የግል ድርጅት በማቋቋም አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ባለሙያዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

   ሀ) ከቦርዱ የተሰጣቸውን የፀና የሙያ ፈቃድ ዋናውን መመለስ፤

   ለ) የሽርክና ማኅበሩ ስለመፍረሱ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

   ሐ) የሽርክና ማኅበሩን ለማፍረስ ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ እስከቀረበበት ቀን ድረስ የሚጠበቅባቸውን ግብር ስለመክፈላቸው የማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ፤

   መ) የሙያ ፈቃዱ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ በሽርክና ማኅበሩ ሥም አገልግሎት የማይሰጡ ስለመሆኑ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤

   ሠ) የሙያ ፈቃድ በመለሱበት በጀት ዓመት ማኅበሩ አገልግሎት የሰጣቸውን የደንበኞች ዝርዝር፣ የተሰጠ የአገልግሎት ዓይነት፣ አገልግሎቱን የሰጠው ሸሪክ ስም እና ቦርዱ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ያካተተ ሰነድ ማቅረብ፤

ረ) የሽርክና ማህበሩ ስለመፍረሱ የሚያረጋገጥ በሚመለከተው አካል የጸደቀ ቃለ-ጉባዔ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ማቅረብ፤ እና

ሰ) እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ ሥር በግል የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ፈቃድ ለመስጠት የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው፡፡

31)**<u>ከኅብረት ሽርክና ማኅበር ወደ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ለውጥ ስለማድረግ</u>**

1) የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት ሲሰጥ የነበረ የኅብረት ሽርክና ማኅበር የንግድ ድርጅት ዓይነት ለውጥ በማድረግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር በማቋቋም አገልግሎት መስጠት ከፈለገ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ለውጥ ማድረግ የሚፈልግ ማኅበር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

   ሀ) የኅብረት ሽርክና ማኅበሩን ወደ ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር ለመቀየር ስምምነት መደረሱን የሚያረጋግጥ በሚመለከተው አካል የጸደቀ ቃለ-ጉባዔ ማቅረብ፤

   ለ) ከቦርዱ የተሰጠውን የፀና የሙያ ፈቃድ ዋናውን መመለስ፤ እና

   ሐ) እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ሁለት ንዑስ ክፍል ሁለት ሥር የሽርክና ማኅበር በማቋቋም የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

32)**<u>ከሽርክና ማኅበር በመውጣት በግል አገልግሎት ስለመስጠት</u>**

1) ከሽርክና ማኅበር በመውጣት የግል ድርጅት አቋቁሞ የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት መስጠት የሚፈለግ ባለሙያ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የግል ድርጅት በማቋቋም አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ ባለሙያዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

   ሀ) ባለሙያው ከማኅበሩ ስለመውጣቱ የሚያረጋግጥ በሚመለከተው አካል የጸደቀ ቃለ-ጉባዔ ማቅረብ፤ እና

ለ) እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ ሥር በግል የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ፈቃድ ለመስጠት የተቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ መሠረት አንድ ሽሪክ ከማኅበሩ ሲወጣ የሽርክና ማኅበሩ የሚከተሉት ግዴታዎች አለበት፡፡

ሀ) ሽሪክ ከማኅበሩ ስለመውጣቱ በ14 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ፤

ለ) በሚመለከተው አካል የጸደቀ ቃለ-ጉባዔ ማቅረብ፤

ሐ) የሥራ አስኪያጅ ለውጥ ካለ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ የተነሳ የፓስፖርት መጠን ያለው ባለቀለም አንድ ፎቶ ግራፍ ማቅረብ፤

መ) ሽሪክ ከማኅበሩ በመውጣቱ ምክንያት በሙያ ፈቃዱ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ለውጥ የሚደረግ ከሆነ ቀድሞ የተሰጠውን ዋናውን መመለስ እና ምትክ ለማግኘት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤ እና

ሠ) ሽሪክ በመውጣቱ ምክንያት ማኅበሩ አንድ አባል ብቻ የቀረው ከሆነ እና ማኅበሩ እንዳይፈርስ የሚፈለግ ከሆነ በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አዲስ ሽሪክ መጨመር አለበት፡፡ በሕግ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሽሪክ ካልተጨመረ የሙያ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

## 33)<u>አዲስ ሽሪክ ስለመቀበል</u>

1) ማንኛውም የሽርክና ማኅበር አዲስ ሽሪክ ሲቀበል የሚከተሉትን ግዴታዎች መፈጸም አለበት፡፡

ሀ) ሽሪኩ ከቦርዱ የተሰጠ የፀና የሙያ ፈቃድ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፤

ለ) አዲስ አባል ስለመቀበሉ በ14 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ፤

ሐ) አዲስ ሽሪክ ለመቀበል ስምምነት ላይ መድረሱን የሚያረጋግጥ በሚመለከተው አካል የጸደቀ ቃለ-ጉባዔ ማቅረብ፤ እና

መ) ማኅበሩ አዲስ ሽሪክ በመቀበሉ ምክንያት በሙያ ፈቃዱ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ለውጥ የሚደረግ ከሆነ ቀድሞ የተሰጠውን ፈቃድ ዋናውን መመለስ እና ምትክ ለማግኘት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል፤

2) ነባር የሽርክና ማኅበር ውስጥ ሽሪክ በመሆን አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ባለሙያ የሚከተሉትን ግዴታዎች መፈጸም አለበት፡፡

   ሀ) የሽርክና ማኅበር ውስጥ ሽሪክ ሆኖ ስለመቀላቀሉ በ14 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ፤

   ለ) የሽርክና ማኅበር ውስጥ ስለመቀላቀሉ ከማኅበሩ ማረጋገጫ ማቅረብ፤

   ሐ) ከቦርዱ የተሰጠውን የፀና የሙያ ፈቃድ ዋናውን መመለስ፤

   መ) የሙያ ፈቃዱ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ በግሉ አገልግሎት የማይሰጥ ስለመሆኑ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፤ እና

   ሠ) የሙያ ፈቃዱን በመለሰበት በጀት ዓመት የነበረውን የደንበኞችን ዝርዝር፣ የሰጠውን የአገልግሎት ዓይነት እና ቦርዱ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን ያካተተ ሰነድ ማቅረብ፡፡

## 34)<u>ከሽርክና ማኅበር በመውጣት በግል ፈቃድ ለማግኘት ማማልከቻ ስለሚቀርብበት ጊዜ</u>

1) ማንኛውም ባለሙያ ከሽርክና ማኅበር በመውጣት በግሉ አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ከሆነ በአንድ መቶ ሰማንያ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ባለሙያው ከማኅበሩ ስለመውጣቱ የተያዘው ቃለ-ጉባዔ አግባብ ባለው የመንግስት አካል ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርብ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም፡፡ ሆኖም ፈቃድ ለማግኘት በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መስፈርቶች በማሟላት አዲስ ማመልከቻ በሚቀርብበት ሥርዓት ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል፡፡

## 35)<u>የሙያ ፈቃድ ስለመመለስ</u>

1) ማንኛውም የሙያ ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት በማናቸውም ምክንያት ሙያዊ አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ የታደሰ የሙያ ፈቃዱን ለተወሰነ ጊዜ ወይም በቋሚነት ለቦርዱ ሊመልስ ይችላል፡፡

2) የሙያ ፈቃድ ለመመለስ የሚያመለክት ባለሙያ ወይም ድርጅት፡-

ሀ) ድርጅቱን ስለመዝጋቱ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ፣

ለ) ከቦርዱ የተሰጠውን የጸና የሙያ ፈቃድ ዋናውን መመለስ፣ እና

ሐ) ድርጅቱን ለመዝጋት ለሚመለከተው አካል ማመልከቻ እስካቀረበበት ቀን ድረስ የሚጠበቅበትን ግብር ስለመክፈሉ ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ አለበት፡፡

3) በዚህ አንቀጽ መሠረት የሙያ ፈቃዱን የመለሰ ባለሙያ ወይም ድርጅት እንደአግባብነቱ ሥሙ ከባለሙያ ወይም ከድርጅት መዝገብ ላይ ይሰረዛል፡፡

4) የሙያ ፈቃዱን የመለሰ ባለሙያ ወይም ድርጅት ፈቃዱን መልሶ ለመውሰድ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ወደ ሥራ ለመመለስ የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) አመልካቹ የሙያ ፈቃዱን ከመለሰ አንድ ዓመት ያላለፈው ከሆነ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል ስድስት መሠረት አንድ ዓመት ያላለፈው የሙያ ማጎልበቻ ሥልጠና መውሰዱን ከሚያስረዳ ማስረጃ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

ለ) አመልካቹ የሙያ ፈቃዱን ከመለሰ አንድ ዓመት ያለፈው ከሆነ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተጠቀሰው በተጨማሪ በቦርዱ ተቀባይነት ያለው የሥራ ልምድ ማቅረብ አለበት፡፡ የሚቀርበው የሥራ ልምድ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ወደ ኋላ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተገኘ እና አመልካቹ ቢያንስ ለስድስት ወራት እንደአግባብነቱ የሒሣብ ወይም የኦዲት ሥራ የሠራ መሆኑን የሚያስረዳ መሆን አለበት፡፡

6) ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈቀደለት ባለሙያ ወይም ድርጅት ለሙያ ፈቃድ ዕድሳት የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 23 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የባለሙያ ወይም የድርጅት ግዴታዎች እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች

### 36) የባለሙያ ወይም የድርጅት ግዴታዎች

በአዋጁ እና በደንቡ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፡፡

1) ቦርዱ ያወጣውን የሙያ ሥነ-ምግባር ደንብ የማክበር፤
2) የኦዲት አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ዓለም አቀፍ የኦዲት እና የማረጋገጥ ደረጃዎች ቦርድ ያወጣቸውን ሁሉንም ደረጃዎች የመከተል፤
3) የሒሣብ ሥራ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ዓለም አቀፍ ኦዲት እና የማረጋገጥ ደረጃዎች ቦርድ ያወጣቸውን ዓለም አቀፍ የክለሳ እና ተዛማጅ ሥራዎች ደረጃዎች እና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች በጥራት አመራር ላይ የመከተል፤
4) ቦርዱ ባከናወነው የኦዲት ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ ግኝት መሠረት የተሰጠውን አስተያየት በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ የማስተካከል፤
5) በዚህ መመሪያ በተለየ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር በባለሙያ ወይም በድርጅት ሥም የሚወጣ ማንኛውም የሒሣብ መግለጫ፣ የማረጋገጫ እና የኦዲት ሪፖርት ከቦርዱ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ ብቻ እንዲፈረም የማድረግ፤
6) ተሳትፎ ባልተደረገበት ወይም እራሱ ባላዘጋጀው የሒሣብ መግለጫ ወይም የኦዲት ሪፖርት ላይ ፊርማ ወይም ማህተም አለማድረግ፤
7) ባለሙያው ከሰጠው ሙያዊ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በቦርዱ ሲጠየቅ ፈጣን፣ ትክክለኛ እና የተሟላ ማብራሪያ የመስጠት እና የመተባበር፤
8) የባለሙያውን ሥራ በተመለከተ የቦርዱ ሠረተኞች የሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ እና የክትትል ሥራ በሚያከናውኑበት ወቅት ምቹ ቢሮ የማዘጋጀት፤
9) የቦርዱ ሠራተኛ ከሥራው ጋር በተያያዘ ለሚጠይቀው ጥያቄ ትክክለኛ መረጃ እና ማብራሪያ የመሥጠት እንዲሁም መረጃዎችን ከመደበቅ የመቆጠብ፤
10) ከደረጃዎች አተገባበር ጋር በተያያዘ ቦርዱ በሚያደርገው የምርመራ ሥራ፣ የክትትል እና የሕግ ማስከበር ሥራ ተባባሪ የመሆን እና መሰናክል ከመፍጠር የመቆጠብ፤
11) ለግብር አስገቢው ባለሥልጣን እና ለሌላ አግባብ ላለው የመንግስት አካል ትክክለኛ መረጃ የመስጠት፤
12) የደንበኛን መረጃ አደራጅቶ የመያዝ፤
13) የሠራተኞቹን መረጃ የመያዝ እና ለቦርዱ የማሳወቅ፤
14) የአድራሻ፣ የድርጅት ሥም እና ማናቸውም መረጃዎች ላይ ለውጦች ሲኖሩ በአስራ አራት ቀናት ውስጥ ለቦርዱ የማሳወቅ፤

15) በማጭበርበር ወይም በማስመሰል ፈቃድ ከመውሰድ፣ ለመውሰድ ከመሞከር፣ ፈቃድ ከማሳደስ ወይም ለማሳደስ ከመሞከር መቆጠብ፤
16) ባልታደሰ የሙያ ፈቃድ ወይም የሙያ ፈቃዱ በታገደበት ወይም በተሰረዘበት ወቅት አገልግሎት አለመስጠት፤
17) የሙያ ፈቃድ ተመላሽ ሳይደረግ በሙሉ ጊዜም ሆነ በትርፍ ሰዓት ተቀጥሮ አለመሥራት፤
18) የሙያ አገልግሎት ከመሰጠቱ በፊት ከደንበኛው ጋር የሙያ አገልግሎት የጽሁፍ ውል የመያዝ፤
19) የሙያ ፈቃዱን ሌላ ሰው እንዲገለገልበት አሳልፎ አለመስጠት ወይም የሙያ ሥራውን በውክልና አለማሠራት፤
20) በሒሣብ ወይም በኦዲት ድርጅት ውስጥ ሸሪክ ከሆነ በግሉ ወይም በሌላ የሽርክና ማኅበር ውስጥ ሸሪክ በመሆን የሒሣብ ወይም የኦዲት አገልግሎት አለመስጠት፤
21) የሙያ ፈቃዱ ከሚፈቅደው የሙያ አገልግሎት ውጪ አለመሥራት፤
22) የሙያ መድን ዋስትና ሳይገባ፣ የአገልግሎት ማስቀጠያ ስምምነት ውል ሳይፈፅም፣ አገልግሎት መስጪያ ቢሮ ሳይኖረው እንዲሁም እንደ አግባብነቱ የኦዲት ቡድን ሳያቋቁም እና የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው አገልግሎት አለመስጠት፤ እና
23) ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት መክፈቱን ለቦርዱ ሳያሳውቅ በቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱ አገልግሎት አለመስጠት፡፡

## 37)<u>የአስተዳደራዊ እርምጃ አፈጻጸም</u>

1) ቦርዱ አዋጁ፣ ደንቡ፣ ይህ መመሪያ እና የሙያ ሥነ-ምግባር ደንቡ በባለሙያ ወይም በድርጅት መጣሱን ሲያረጋግጥ በአዋጁ እና በደንቡ የተቀመጡትን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡፡
2) በቦርዱ የተወሰነ ማንኛውም የቅጣት ውሳኔ በባለሙያው ወይም በድርጅቱ የግል ማኅደር ውስጥ እንዲመዘገብ ወይም እንዲያያዝ ይደረጋል፡፡
3) የሙያ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት ቦርዱ የዕገዳ ወይም የስረዛ ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ከቦርዱ የተሰጠውን የሙያ ፈቃድ ለቦርዱ መመለስ አለበት፡፡

4) በዚህ መመሪያ መሠረት ቦርዱ የሙያ ፈቃድ ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ባለሙያው ወይም የድርጅቱ ሸሪኮች አባል ለሆኑበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ፣ የንግድ ፈቃድ ለመስጠትና ለመቆጣጠር ኃላፊነት ለተሰጠው አካል፣ ለገቢዎች ሚኒስቴር እና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካላት በፅሑፍ ያሳውቃል፡፡

38)<u>ስለ ሙያ ፈቃድ ዕገዳ</u>

1) የሙያ ፈቃድ ዕገዳ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን ከአንድ መቶ ሰማንያ ተከታታይ ቀናት ሊበልጥ አይችልም፡፡
2) የሙያ ፈቃዱ በቦርዱ የታገደበት ባለሙያ ወይም ድርጅት የዕገዳ ጊዜው ሲያበቃ ወደ ሥራ ለመመለስ በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ማመልከት አለበት፡፡
3) ቦርዱ ማመልከቻውን ተቀብሎ ከመረመረ በኋላ ለዕገዳው ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በአግባቡ መስተካከላቸውን ካመነ ወደ ሥራ እንዲመለስ ሊፈቅድ ይችላል፡፡
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሥራ ለመመለስ ካላመለከተ ወይም ለዕገዳው ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች መስተካከላቸው ካልታመነ የሙያ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡
5) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ማመልከቻ ያልቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነ በአንድ መቶ ሰማንያ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ወደ ሥራ ለመመለስ ማመልከቻ ሊቀርብ ይችላል፡፡
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የቀረበ ማመልከቻ በዋና ዳይሬክተሩ ተቀባይነት ካገኘ እና ለዕገዳው ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች በአግባቡ መስተካከላቸው ከታመነ ስረዛው ሊነሳ ይችላል፡፡

39)<u>ወደ ሥራ ስለመመለስ</u>

1) የሙያ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሙያ ወይም ድርጅት በድጋሚ ወደ ሥራ ለመመለስ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ፣ ሁለት እና ሦስት ድንጋጌዎች መሠረት እንደ አዲስ ማመልከት አለበት፡፡
2) የባለሙያው ወይም የድርጅቱ ፈቃድ የተሰረዘው በክስ ሰሚዎች ውሳኔ ከሆነ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሦስት ዓመታት ውስጥ እንደ አዲስ ማመልከት

አይችልም፡፡ ሆኖም የምሥክር ወረቀቱ የተሰረዘው በወቅቱ ባለመታደሱ ከሆነ የምሥክር ወረቀቱ ከተሰረዘበት ከአንድ ዓመት በኋላ እንደ አዲስ ማመልከት ይችላል፡፡

40)**<u>የዲሲፕሊን ቅጣት ሪከርድ</u>**

አንድ ባለሙያ ወይም ድርጅት በክስ ሰሚዎች ውሳኔ በዲሲፕሊን ከተቀጣ በኋላ ቅጣቱ በሪከርድነት ሊቆይ እና ሊጠቀስበት የሚችለው፡-

1) በተግሳጽ ወይም በማስጠንቀቂያ ብቻ የተቀጣ ከሆነ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት፣
2) ከተግሳጽ ወይም ከማስጠንቀቂያ ውጪ በሌላ ቅጣት ከተቀጣ ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለሁለት ዓመት፣

ነው፡፡

41)**<u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>**

1) ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት በአድራሻ፣ በድርጅት ሥም፣ በአደረጃጀት እና በሌሎች መረጃዎች ላይ ያደረገውን ለውጥ በአስራ አራት ቀናት ውስጥ ለቦርዱ አለማሳወቅ በገንዘብ ያስቀጣል፡፡
2) ማንኛውም ባለሙያ ወይም ድርጅት ያደረገውን ለውጥ በአስራ አራት ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ካላሳወቀ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀን ብር አምስት መቶ (500.00) ቅጣት ይከፍላል፡፡
3) ባለሙያው ወይም ድርጅቱ ለውጡን በአስራ አራት ቀናት ውስጥ አለማሳወቁ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መጉላላት ወይም ጉዳት ያደረሰ ከሆነ ወይም በቦርዱ የክትትል ሥራ ላይ እንቅፋት የፈጠረ ከሆነ ወይም ለውጡን ከስድስት ወራት በኋላ ለቦርዱ ያሳወቀ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከሚጣልበት የገንዘብ ቅጣት በተጨማሪ በዲሲፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡
4) ባለሙያው ወይም ድርጅቱ ያደረገው ለውጥ የታወቀው ቦርዱ በሚያደርገው የክትትል ሥራ ወይም በሦስተኛ ወገን ጥቆማ ከሆነ ከዘገየበት ቀን ጀምሮ ለውጡ በቦርዱ እስከታወቀበት ቀን ድረስ ለእያንዳንዱ ቀን አንድ ሺህ ብር (1,000.00) ቅጣት ይከፍላል፡፡ በተጨማሪም በዲሲፕሊን ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 42)<u>የቅንጅት እና የትብብር ሥራዎች</u>

1) ቦርዱ በኦዲተሮች ላይ የኦዲት ሥራ ጥራት ማረጋገጫ ምርመራ በሚያከናውንበት ወቅት ጉልህ ጥፋት መፈጸሙን ካረጋገጠ ባለሙያው ወይም የድርጅቱ ሽሪኮች አባል ለሆኑበት የሒሣብ ሙያ ማኅበር፣ ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ እና ለሌሎች የመንግሥት ተቆጣጣሪ አካላት በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡
2) ቦርዱ ከዲሲፕሊን ጥፋት ጋር በተያያዘ በፐብሊክ ኦዲተር ላይ የተወሰደ እርምጃን የሕዝብ ጥቅም ያለባቸውን ሪፖርት አቅራቢ አካላት ለሚቆጣጠር አካል በፅሑፍ ያሳውቃል፡፡
3) በአዋጁ አንቀጽ 37 በተደነገገው መሠረት የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል ተቆጣጣሪ የሆነ እንደ የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና መሰል የመንግሥት መሥሪያ ቤት ኃላፊ አዋጁ ወይም በአዋጁ መሠረት የወጣ ደንብ ወይም መመሪያ የሚጥስ ተግባር በፐብሊክ ኦዲተር ተፈጽሟል ብሎ ሲያምን ለቦርዱ በፅሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
4) የአዋጁ እና የደንቡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ወቅታዊ የሆነ የሒሣብ እና የኦዲት ባለሙያዎችን ሥም ዝርዝር ለባለድርሻ አካላት በተለይም ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ለኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፣ ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ፣ ለገቢዎች ሚኒስቴር እና ለሌሎች ተቆጣጣሪ መንግሥታዊ አካላት በየዓመቱ ያሳውቃል፡፡

# <u>ክፍል አምስት</u>

# <u>የሒሣብ ሙያ ማኅበራት አክሬዲቴሽን እና ዕውቅና</u>

## 43)<u>በአገር ውስጥ ለተቋቋመ የሒሣብ ሙያ ማኅበር አክሬዲቴሽን ስለመስጠት</u>

1) ቦርዱ በአዋጅ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መሥፈርቶች ላሟላ አገር በቀል የሒሣብ ሙያ ማኅበር እና ቅርንጫፉ እንደ ሒሣብ ሙያ ማኅበር የአክሬዲቴሽን ምስክር ወረቀት ይሠጣል፡፡
2) የሒሣብ ሙያ ማኅበሩ እና ቅርንጫፉ አክሬዲቴሽን ለማግኘት በአዋጁ አንቀጽ 26 ከተደነገገው በተጨማሪ፡-

ሀ) የሒሣብ ሙያ ማኅበሩ ዓለም አቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ሙሉ አባል የሆነ ወይም ለመሆን የሚያስችለውን ፕሮግራም ቀርፆ የሚንቀሳቀስ ስለመሆኑ ማስረጃ፤

ለ) በፋይናንስም ሆነ በአሠራሩ ረገድ ፀንቶ በሥራ ላይ የቆየ ወይም ለመቆየት የሚያስችለው ፕሮግራም ያለው እና ለወደፊትም እንደሚቀጥል ሊገመት የሚችል ስለመሆኑ ማስረጃ፤

ሐ) ቢሮ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማረጋገጫ፤

መ) የማቋቋሚያ ሕግ (ኮንስቲትዩሽን) ወይም የመመስረቻ ቃለ-ጉባዔ ወይም ጽሁፍ ሰነድ፤

ሠ) የመተዳደሪያ ደንብ፤

ረ) የቀጣይነት የአጭርና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂ ዕቅድ እና የመፈጸም አቅምን የሚያሳይ ሰነድ፤

ሰ) ትርፍና ኪሳራ እንዲሁም ሀብትና እዳ የሚገልጽ ሪፖርት፤

ሸ) የአባላቱን ብዛትና ጾታ የሚያሳይ መረጃ፤

ቀ) ድርጅታዊ መዋቅሩን የሚያሳይ በጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀ ሰነድ፤

በ) የማኔጅመንት ወይም የአመራር ብዛት፤

ተ) በቋሚነት የቀጠራቸው ሠራተኞች ብዛት የሚያሳይ መረጃ፤ እና

ቸ) አክሪዲቴሽን የተጠየቀው ለቅርንጫፍ ከሆነ ለቦርዱ ማመልከቻ ከመቅረቡ በፊት የሒሣብ ሙያ ማኅበሩ ምክር ቤት ቅርንጫፍ ለመክፈት የወሰነ ስለመሆኑ ማስረጃ፤

ማቅረብ አለበት፡፡

## 44)<u>በውጭ አገር ለተቋቋመ የሙያ ማኅበር ዕውቅና ስለመስጠት</u>

1) በውጪ አገር የተቋቋመ የሒሣብ ሙያ ማኅበር እና ቅርንጫፉ በአዋጅ እና በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን መሥፈርቶች ማሟላቱ በቦርዱ ሲረጋገጥ እንደ ሒሣብ ሙያ ማኅበር የዕውቅና የምሥክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡፡

2) የሒሣብ ሙያ ማኅበሩ እና ቅርንጫፉ ዕውቅና ለማግኘት በአዋጁ አንቀጽ 26 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2 ከፊደል (ሐ) እስከ (ቸ) ከተደነገገው መስፈርት በተጨማሪ፡-

   ሀ) የሒሣብ ሙያ ማኅበሩ የዓለም ዓቀፍ የሒሣብ ባለሙያዎች ፌደሬሽን ሙሉ አባል ስለመሆኑና የአባልነት ግዴታውን ስለማክበሩ፤ እና

   ለ) በፋይናንስም ሆነ በአሠራሩ ረገድ ፀንቶ በሥራ ላይ የቆየና ለወደፊትም እንደሚቀጥል ሊገመት የሚችል ስለመሆኑ፤

   ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

## 45)<u>አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

1) ቦርዱ እንደ ሒሣብ ሙያ ማኅበር አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና እንዲሰጠው የሚፈልግ በአገር ውስጥ ወይም በውጪ አገር የተቋቋመ የሒሣብ ሙያ ማኅበር እና ቅርንጫፉ ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ እና እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 ወይም 44 ሥር የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሟላቱን ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡

## 46)<u>አክሬዲቴሽን ወይም ዕውቅና ይዞ ስለመቀጠል</u>

1) ማንኛውም የሒሣብ ሙያ ማኅበር የተሰጠውን አክሬዲቴሽን ወይም እውቅና ይዞ ለመቀጠል ቦርዱ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከተገቢው የአገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ እና በአዋጁ አንቀጽ 27 እንዲሁም እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 እና 44 ሥር የተዘረዘሩት መስፈርቶች ማኅበሩ ጠብቆ መቆየቱን ከሚያስረዱ ማስረጃዎች ጋር ቦርዱ በዘረጋው የአሰራር ሥርዓት መሠረት መቅረብ አለበት፡፡
3) ዕውቅናን ወይም አክሬዲቴሽንን ይዞ ለመቀጠል የሚቀርብ ማመልከቻ የሙያ ማህበሩ የሒሣብ ዓመት ባለቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
4) ዕውቅናን ወይም አክሬዲቴሽንን ይዞ ለመቀጠል የቀረበን ማመልከቻ ቦርዱ ሳያይ ጊዜው ካለፈ ማመልከቻውን አይቶ እስኪወስን ድረስ ዕውቅናው ወይም አክሪዲቴሽኑ የሚቀጥል

ሆኖ ማመልከቻው ተቀባይነት ሲያገኝ እውቅናው ወይም አክሪዲቴሽኑ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ካለቀበት ቀን ጀምሮ እንደሚያገለግል ይቆጠራል፡፡

5) ማንኛውም የሒሣብ ሙያ ማኅበር የተሰጠውን አክሬዲቴሽን ወይም እውቅና ይዞ ለመቀጠል በአዋጁ አንቀጽ 27 እና እንደአግባብነቱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 2 አክሪዲቴሽን ወይም ዕውቅና ለማግኘት የተቀመጡትን መስፈርቶች ጠብቆ መገኘት አለበት፡፡

6) ማንኛውም የሒሣብ ሙያ ማኅበር በዚህ አንቀጽ መሠረት ዕውቅናን ወይም አክሬዲቴሽንን ይዞ ለመቀጠል የሚያስችል ፈቃድ ካላገኘ እውቅናው ወይም አክሬዲቴሽኑ ይሰረዛል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 47)ክትትል አለማድረግ

አንድ አመልካች ለቦርዱ ማመልከቻ ካቀረበ በኋላ ቦርዱ እንዲያሟላ የሚጠይቀውን ማስረጃ በስድሳ ተከታታይ ቀናት ውስጥ አሟልቶ ካላቀረበ ማመልከቻው ውድቅ ይደረጋል፡፡ ሆኖም አመልካቹ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል በድጋሚ ሊያመለክት ይችላል፡፡

### 48)ተመላሽ ስለማይደረግ ክፍያ

በዚህ መመሪያ መሠረት ለሚሰጥ ማንኛውም አገልግሎት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ማመልከቻው ተቀባይነት ቢያገኝም ባያገኝም ለአመልካቹ ተመላሽ አይደረግም፡፡

### 49)የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ለማንኛውም የሕዝብ ጥቅም ያለበት አካል የኦዲት እና ማረጋገጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ የተመሠከረለት ኦዲተር ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት የስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በዚህ መመሪያ ለፐብሊክ ኦዲተር የተቀመጡትን መስፈርቶች በማሟላት የፐብሊክ ኦዲተር ፈቃድ ካልወሰደ በስተቀር የሕዝብ ጥቅም ላለበት አካል የኦዲት እና ማረጋገጥ አገልግሎት እየሰጠ መቀጠል አይችልም፡፡

2) ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ከቦርዱ የሒሣብ ወይም የኦዲት ፈቃድ የተሰጠው ባለሙያ ወይም ድርጅት ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው የስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደ አግባብነቱ በዚህ መመሪያ ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና ሁለት ሥር የተቀመጠውን የሙያ መድን ዋስትና እና የኦዲት ቡድን የማቋቋም ግዴታ በማሟላት ለቦርዱ ማስረጃ ካላቀረበ የሙያ ፈቃዱ ይሰረዛል፡፡

50)<u>**ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**</u>

1) የሒሣብ እና የኦዲት ባለሙያዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና የሒሣብ ሙያ ማኅበራት ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 805/2013 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2) የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

51)<u>**መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ**</u>

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ከተመዘገበ እና በኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝ እና ኦዲት ቦርድ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 08 ቀን 2017 ዓ.ም**

**ኢዮብ ተካልኝ (ፒ.ኤች.ዲ.)**

**የኢትዮጵያ የሒሣብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ**